

፩ ኮሚዩኒቲ



# አንድ የኢትዮጵያውያን ኮሚዩኒቲ ብቻ !!

# የጃንዋሪው ሕዝባዊ ስብሰባ ውሳኔ ይከበር!!

ጃንዋሪ 16, 2011 በዴንቨር ኮሎራዶ፣ በአውሮራ ክ/ከተማ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲን ለመመስረት በራሳቸው አነሳሽነት በተሰባሰቡ ግለሰቦች የተጠራ ስብሰባ ተደርጎ እንደነበር የሚታወስ ነው። ተሰብሳቢው በዕለቱ የተደረገውን ሰብሰባ ሲያጠቃልል፣ ስብሰባውን የጠሩትን ሰዎች አመስግኖ፣ የስብሰባው አዘጋጆችና ነባሩ ኮሚቴ በጋራ በመሆን፣ ቢቻል በ6 ወር ጊዜ ውስጥ የኮሙኒቲውን የቦርድ አባላት አስመርጥው፣ በነባሩ የኮሚዩኒቲ አመራር እጅ የሚገኘውን ማሕተምና ልዩልዩ ዶኩሜንቶች አዲስ ለሚመረጠው ቦርድ እንዲያስረክቡ ስብሰባው መወሰኑ ይታወሳል።

ይሁን እንጂ፣ የስብሰባው አዘጋጆች በስብሰባው የተሰጠውን ውሳኔ ወደጎን በመተው፣ በመታወቂያ ቁጥር 20111083841 "Ethiopian People Community of Colorado" - በኮሎራዶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኮሚዩኒቲ - በሚል ስያሜ፣ በአቶ አብርሃ በየነ ስም፣ ፌብሩዋሪ 9, 2011 በኮሎራዶ ስቴት ቢሮ አዲስ ኮሚዩኒቲ ማስመዝገባቸውን ተረድተናል። ይህንኑ መነሻ በማድረግ በጃንዋሪው ስብሰባ የተሰጠው ውሳኔ ተጥሷል በሚል ፌብሩዋሪ 27, 2011 ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ግለሰቦች የተገኙበት ስብሰባ በማድረግ የነባሩ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ሰብሳቢ የሆኑትን ወ/ሮ ሰናይት ከተማን ጠርቶ ማብራሪያ ጠይቋል።

ወ/ሮ ሰናይት ባቀረቡት ገለጻ የስብሰባው አዘጋጆች ለስብሰባ ጠርተዋቸው በእጃቸው የሚገኘውን ማሕተምና ልዩልዩ ዶኩሜንቶች እንዲያስረክቡ መጠየቃቸውንና በእዚህ ጉዳይ ላይ ወደ ሁለት ሰዓታት እንደተነጋገሩበት አስረድተዋል። በመጨረሻም ቡድኑ የራሱን ስብሰባ አድርጎ የእኛ ከእነርሱ ጋር መሳተፍ ጥቅም የሚሰጥ መስሎ ካገኘው ለሌላ ስብሰባ እንደሚጠራን፣ አለበለዚያ ግን ስሙን በመቀየር ሌላ ማህበር እንደሚያቋቁም ነግረውን አሰናብተውናል፣ በማለት ገለጻቸውን አጠቃለዋል። እንደወ/ሮ ሰናይት ገለጻ ከሆነ፣ ላልተመረጠ አካል የተባሉትን ዶኩሜንቶች ማስረከቡ ከሕዝቡ የተሰጣቸውን ውሳኔ እንደመሻር መስሎ ስለታያቸው ሳያስረከቡ ተመልሰዋል።

ስብሰባው የወ/ሮ ሰናይትን ገለጻ ካዳመጠ በኋላ፣ ከዚህ በፊት የነበረውን ኮሚውኒቲ ሁሉን አቀፍ በሆነ መልክ አጠናክሮ መላውን የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ በስፋት ለማገልገል በሚያስችል መልኩ ለማደራጀት "፩ ኮሚዩኒቲ" በሚል ስያሜ ዘጠኝ አባላት ያሉት ግብረሀይል አቋቁሞ ውሳኔዎችን አስተላልፏል።

- ነባሩ ኮሚዩኒቲ ዶኩሜንት ላለማስረከብ የወሰደው አቋም አግባብና ሕጋዊነት ያለው መሆኑን ተስማምቶበታል፣ ወ/ሮ ሰናይት ለወሰዱትም አስተዋይነት የተመላበት እርምጃ ከፍተኛ ምስጋና አቅርቧል፣
- በሕጋዊ መንገድ የተመረጠ ቦርድ ሳይኖርና፣ በሕዝብ ምርጫ የተሰጠ ሕጋዊ ውክልና ሳይኖር አዲሱ ቡድን የኮሚዩኒቲ ፍቃድ ማውጣቱና ማስመዝገቡ፣ እንዲሁም ገንዘብ ለማሰባሰብና መሰል ተግባራትን ለመፈጸም መንቀሳቀሱ አግባብነት የሌለው መሆኑንና የጃንዋሪው ስብሰባ ውሳኔ እንዳልነበረም አስምሮበታል፣
- በክልላችን ከአንድ ኮሚውኒቲ በላይ ማቋቋሙ የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት መባከንን ስለሚያስከትል <u>አስገዳጅ ሁኔታ ካልተፈጠረ በቀር</u> አንድ የተጠናከረ ኮሚውኒቲ ብቻ ለማቋቋም ጥረት እንዲደረግ ተስማምቷል፣
- ጃንዋሪ 16, 2011 ስብሰባ የጠራው ቡድን በሕዝብ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት፣ ከነባሩ ቦርድ ጋር በመሆን በሕዝብ ለሚመረጥ አመራር አስረክቦ እንዲሰናበት "፩ ኮሚዩኒቲ" ያልተቆጠበ ጥረት እንዲያደርግ ወስኗል፣
- በራስ ተነሳሽነት የሚደረግ ጥረት ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ቢታመንም፣ በአንድ ወይም በሌላ የሃይማኖት፣ የጎሳ፣ የፖለቲካ ድርጅት ተፅእኖ ስር የመውደቅ አደጋም ሊያጋጥመው ስለሚችል ሁሉን አቀፍ ሆኖ እንዲቋቋም ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ስብሰባው አምኖበታል። ኮሚዩኒቲውን ለማደራጀት የሚንቀሳቀሱ አካላት፣ ያገባኛል፣ ይመለከተኛል ብሎ የሚቀርበውን፣ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን ግለሰብ ሁሉ ማቀፍና ማሳተፍ እንዳለባቸው አሳስቧል።
- "፩ ኮሚዩኒቲ"ም ይህንኑ መርህ ተከትሎ እንዲቀሳቀስ ወስኗል።

<u>ውድ ኢትዮጵያውያን፤</u>

የአብራችሁ ስሩ ጥሪያችሁን ግብ ለማድረስ እና በየተቋማቱ የሚታየውን ለሁለት የመከፋፈልን መጥፎ አባዜ ለማስወገድ አሁን የተቋቋመው "፩ ኮሚዩኒቲ" የተሰኘው ጊዜያዊ ግብረሀይል ከሁሉም ባለጉዳዮች ጋር በመመካከር አንድ የተጠናከረ ኮሚዩኒቲ ለመመስረት ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል፣

- "፩ ኮሚዩኒቲ" አዲስ የተመዘገበውን ቡድን ከነባሩ ጋር በማነጋገርና በማወያየት ነባሩን አጠናክሮ አንድ ውሁድ ኮሚዩኒቲ ለመፍጠር ይጥራል፣ ያግዛል፤
- "፩ ኮሚዩኒቲ" የጀመረውን ጥረት ለማገዝ የሚረዱ ማናቸውንም ገንቢ አስተያየቶች ይቀበላል፤ ለዚሁም ሲባል ከታች የተመለከቱትን የመልእክት መቀበያ ስልክና ኢሜል አዘጋጅቷል፤
- "፩ ኮሚዩኒቲ" በኮሚቴ መልክ ኮሚዩኒቲውን የማጠናከር ስራውን ካከናወነ በኋላ ይከስማል፤

**ጥያቄ ወይም ገንቢ አስተያየት ካለዎ ይደውሉልን፣ የኢሜል መልእክት ይላኩልን**

ስልክ፡ 720 443 7797

ኢሜል፡ **one_ethiopian_community@yahoo.com**

# <u>አንድነት ሀይል ነው!!</u>

ማርች፤ 2011